


# የኢየሱስ ክርስቶስ ማንነት

# The Person of Christ (Christology)

*ከዚችም ዓለም ገዦች አንዱ እንኳ ይህን ጥበብ አላወቀም፤ አውቀውስ ቢሆኑ የክብርን ጌታ ባልሰቀሉትም ነበር።*
*(1ቆሮ 2:8)*

*በዳዊት ፋሲል*

*2003 ዓ.ም.*

# የኢየሱስ ክርስቶስ ስሞችና መጠርያ ማዕረጐች

**ኢየሱስ:-** የግሪክ ቃል ሲሆን "መድኃኒት፣ አዳኝ" ማለት ነው::
በዕብራይስጥ "የሹዋህ" Yeho-shuah ትርጉሙ "ያህዌ" አዳኝ ነው፣ "እግዚአብሔር አዳኝ ነው" ማለት ነው:: (ማቴ 1:21)

**ክርስቶስ:-** የተቀባ፣ የተሾመ ማለት ነው፣ ይህም የተላከበትን ዓላማና ሥራ ሁሉ ለመፈጸም ሥልጣን እንዳለው የሚገልጥ ማረጋገጫ የሥልጣን ስም ነው:: ክርስቶስ ከስምነት ይልቅ የኢየሱስን ማዕረግ እና ስልጣንን ይገልጣል:: (ማቴ 16:16, ሐዋ 2:36)

**አማኑኤል:-** "ትሥጉትን" (አምላክ በሥጋ መገለጡን) እና በሕዝቡ መካከል መኖሩን የሚገልጥ ስም ነው:: ትርጉሙም "እግዚአብሔር ከእኛ ጋር" ማለት ነው (ኢሳ 7:14, ማቴ 1:23)

**የእግዚአብሔር ልጅ:-** ዘለዓለማዊ የእግዚአብሔር የባህርይ ልጁ፣ ማለትም ፍጹም አምላክ መሆኑን የሚገልጥ መጠሪያ ነው:: (ማቴ 16:16, ዮሐ 20:31)

**የሰው ልጅ:-** በሥጋ መገለጡንና፣ በሥጋና በደም ከእኛ ጋር የተካፈለበትን ፍጹም ሰውነቱን የሚገልጥበት መጠሪያ ነው:: (ማር 10:45, ማቴ 26:64)

**ጌታ:-** በግሪኩ ኩሪዮስ የሚለው ቃል የተተረጐመው "ላለና ለነበረው" ለአምላክ ስም ያህዌህ ለሚለው ሲሆን በግሪኩ መጽሐፍ ቅዱስ ፈጣሪና፣ ፍጥረቱን መጋቢ ለሆነ አምላክ የሚቀጸል መጠሪያ ነው:: (ዮሐ 13:13, ሐዋ 2:36)

**መምህር:-** ከእግዚአብሔር ዘንድ ለሕዝቡ ለእሥራኤል ለአህዛብ ሁሉን ይገልጥ ዘንድ የተላከ ታላቅ አስተማሪ መሆኑን የሚያሳይ (ዮሐ 3:2, ሉቃ 2:29-32, ዮሐ 13:13)

**ንጉሥ:-** በዳዊት ዙፋን ላይ የሚቀመጥበት፣ በያዕቆብ ቤት ሁሉ ላይ፣ በኢየሩሳሌም በታላቁ ንጉሥ ከተማ የሚነግሥበት ሥልጣኑን የሚያሳይ መጠርያ ነው (የሺው ዓመት መንግሥትን አጥና) ማቴ 2:1-11, 27:37

**የዳዊት ልጅ:-** እግዚአብሔር ለዳዊት በዙፋኑ ላይ ለዘላለም የሚቀመጥ ልጅ እንደሚያስነሳለት ተስፋ ሰጥቶታል እናም አይሁድ ሁሉ ተስፋ የሚያደርጉት ንጉሣቸው መሆኑን የሚገልጥ መጠርያ ነው:: (መዝ 89:28-37 ማቴ 1:1, ማር 10:48)

## ሌሎች መጠርያዎች

| | |
|---|---|
| የንጋት ኮከብ | ዘኍ 24:17, ራዕ 22:16 |
| ታላቅ ነቢይ | ዘዳ 18:18, ማቴ 21:11 |
| የማዕዘን ራስ ድንጋይ | ኤፌ 2:20, 1ጴጥ 2:6 |
| አለት | ማቴ 16:16-18, 1ቆሮ 10:4 |
| ቃል | ዮሐ 1:1, 14, 1ዮሐ 1:1, ራዕ 19:13 |

# የክርስቶስ ማንነት (The Person of Christ)

"ኢየሱስ ክርስቶስ ፍፁም አምላክ፣ ፍፁም ሰው በአንድ አካል ነበረ፣ አሁንም እንዲሁ ነው፣ ወደፊትም ለዘለዓለም እንዲሁ ሆኖ የሚኖር ነው::"

## ክፍል ፩

## <u>የኢየሱስ ክርስቶስ ሰብዓዊነት (ሰው መሆን)</u>

### <u>ማረጋገጫ</u>

1.1 <u>በድንግልና መወለድ</u>:- ድንግል ከነበረችው ከማርያም፣ በተዓምራዊ ሁኔታ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ያለሰብዓዊ አባት ተጸነሰ፣ (ማቴ 1:18,20)

- ✓ በድንግልና መጸነሱ ብቻ ሳይሆን በድንግልና መወለዱም ለትንቢቶች መፈጸም አስፈላጊ ነበር:: (ኢሳ 7:14, ማቴ 1:24-25)
- ✓ በመሆኑም ሕፃኑ ኢየሱስ ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጅ ነበረ (ሉቃ 1:34-34)

<u>በድንግልና ያለወንድ ዘር የመወለዱ አስፈላጊነት</u>

ሀ. ደህንነት ፈጽሞ የሚመጣው ከእግዚአብሔር ብቻ ነው::

- ✓ ሰው በራሱ ጥረት እና ፍላጐት ፈጽሞ መዳን አይችልም ስለሆነም የእግዚአብሔርን በጸጋ ማዳን መጠበቅ ብቻ ነበረበት (ገላ 4:4-5)

ለ. ፍጹም አምላክነትና ፍጹም ሰውነት መዋሀድ የሚችሉበት ብቸኛ መንገድ ነው::

- ✓ ኢየሱስ ያለምድራዊ ወላጅ ከሰማይ ሥጋ እንደለበሰ ሙሉ ሰው ሆኖ ቢገለጥ እንደኛ ያለ ፍጹም ሰው መሆኑን ማረጋገጥ አይቻልም::
- ✓ ኢየሱስ ከእናትና አሥጋ አባት እንደኛ የተወለደ ቢሆን ኖሮ ፍጹም አምላክ መሆኑን ፈጽሞ ማረጋገጥ አይቻልም::

ሐ. ፍጹም ሰውነቱና ከኃጢአት ዘር ነፃ መሆኑ የተረጋገጠበት ነው::

- ✓ ኢየሱስ እንደሌሎች የሰው ዘሮች ከአዳም የተቀጠለ የዘር ተዋረድ የለበትም:: ዘር የሚቆጠረው በወንድ እንጂ በሴት በኩል እንዳይደለ ልብ ይሏል::
- ✓ ድንግሊቱ ማርያም ኃጢአት ቢኖርባትም እንኳ ወደ ኢየሱስ ፈጽሞ መተላለፍ እንዳይችል መንፈስ ቅዱስ የመጸለል (የመጋረድ) ሥራ ሠርቷል (ሉቃ 1:35)

## 1.2 የኢየሱስ ክርስቶስ ሰብዓዊ (የሰውነት) ባህርያት

ሀ. ኢየሱስ የሰው አካል ለብሷል

- ✓ እንደ ሕፃን ተወልዷል (ሉቃ 2:7) እንደልጆች በጥበብ፣ በዕውቀት፣ በቁመት ያድግ ነበር (ሉቃ 2:40,52)
- ✓ ይደክመው ነበር (ዮሐ 4:6) ይርበው ነበር (ማቴ 4:2) ይጠማው ነበር (ዮሐ 19:28) መላዕክት ያገለግሉት ነበር (ማቴ 4:11) ነፍሱን በእግዚአብሔር እጅ ላይ አደራ ሰጠ (ሉቃ 23:46)
- ✓ ከሞትም ሲነሳ ሰብዓዊ አካሉ በሙሉ በትንሣኤ አካል ተነስቷል:: ስለሆነም ሥጋና አጥንት ያለው አካል እንጂ መንፈስ አልነበረም (ሉቃ 24:39) በፊታቸውም ምግብ በልቷል (ሉቃ 24:42, ዮሐ 20:17, 20, 27, ዮሐ 21:9, 13)
- ✓ ያው የተነሣ አካል ራሱ ሁሉም እያዩት ወደ ሰማይ ወጥቷል (ሐዋ 1:9) በመሆኑም ኢየሱስ የሚመጣው በአካል እንጂ በመንፈስ አይደለም::

ለ. ኢየሱስ ሰብዓዊ አእምሮ አለው

- ✓ በጥበብ ያድግ ነበር (ሉቃ 2:52)
- ✓ እንደሌሎች ልጆች ሁሉ መብላት፣ መጠጣት፣ መራመድ፣ ማንበብ ወዘተ እየተማረ አደገ፣ የሚያዘው እርሱ መታዘዝን ተማረ (ዕብ 5:8)

ሐ. ኢየሱስ ሰብዓዊ የነፍስ ስሜት ነበረው

- ✓ ነፍስ 3 ክፍሎች አሏት
  1. ስሜት
  2. ፈቃድ
  3. ዕውቀት
- ✓ ነፍሱ ትታወክ ነበር (ዮሐ 12:27) , በመንፈሱ ይታወክ ነበር (ዮሐ 13:21) ነፍሱ ታዝን ነበር (ማቴ 26:38) , ይደነቅ ነበር (ማቴ 8:10)
  ያዝንና ያለቅስ ነበር (ዮሐ 11:35), በመራራ ጩኸትና እንባ ይጸልይ ነበር (ዕብ 5:7)

## 1.3 ኢየሱስ ክርስቶስ ኃጢአት ፈጽሞ የሌለበት ብቸኛው ሰው

- ✓ ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም ሰው ሲሆን ከተበላሸው የሰው ዘር ሁኔታ የሚለየው ፈጽሞ ኃጢአትን ባለማድረጉ ነው::
  - እግዚአብሔር ሰውን *መጀመሪያ* በፈጠረው ጊዜ ሰው ኃጢአተኛ አልነበረም ነገር ግን ሰውየው ፍጹም ሰው ነበረ:: ስለሆነም ኢየሱስ እንደመጀመርያው ሰው ከኃጢአት ነጻ የሆነ ፍጹም ሰው ነው ማለት ነው::
- ✓ የዓለም ብርሃን ነኝ (ዮሐ 8:12) ብርሃን የእውነተኛነትና የንጽህና መገለጫ ነው::
- ✓ ደስ የሚያሰኘውን ሁልጊዜ አደርጋለሁ (ዮሐ 8:29) የአባቱን ትዕዛዝ ሁሉ ይፈጽም ነበር (ዮሐ 15:10), ጲላጦስ ምንም በደል አላገኘበትም (ዮሐ 18:38)
- ✓ በኃጢአተኛ *ሥጋ* ምሳሌ እንጂ ኃጢአተኛ ሆኖ አልተገለጠም (ሮሜ 8:3)
- ✓ ኃጢአት አያውቀውም ነበር (2ቆሮ 5:21) ቢፈተንም ኃጢአትን ከቶ አላደረገም (ዕብ 4:15) እርሱ በክፉ አይፈተንምና (ያዕ 1:13)
- ✓ ቅዱስ እና ነውር የሌለበት፣ ከኃጢአተኞች የተለየ ፍጹም ሰው ነበር (ዕብ 7:26, 1ጴጥ 1:19, 1ጴጥ 2:22, 3:18, 1ዮሐ 2:1, 3:5)
- ✓ የመፈተኑ አስፈላጊነት እኛን ይረዳን ዘንድ ነው (ዕብ 2:18)

## 1.4 የኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም ሰውነት ለምን አስፈለገ?

- ✓ ሐዋርያው ዮሐንስ መልዕክቶቹን የጻፈው ኢየሱስ ፍጹም ሰው አይደለም የሚል የክህደት ትምህርት በተነሳ ጊዜ ነበር:: (1ዮሐ 4:2-3)
  - ዶሴቲዝም (Docetism):- ዶኪዮ በግሪክ መቅረብ፣ መምሰል ማለት ሲሆን ኢየሱስ ሰውን መሰለ እንጂ ሰው አይደለም የሚል የፍልስፍና ትምህርት ነው::

# የኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም ሰው የመሆን አስፈላጊነት

## ሀ. በምትክነት ለመታዘዝ (For representative obedience)

- አዳም የሰው ዘሮችን ሁሉ በመወከል ባለመታዘዝ ኃጢአትን አደረገ በመሆኑም ሁሉም ሰው በአዳም መተላለፍ ምክንያት ኃጢአትን አድራጊና ተላላፊ ሆነ:: (ዘፍ 2:15-3:7) የአዳም መተላለፍና መውደቅ

ሦስቱ የኃጢአት መግቢያ መንገዶች (1ዮሐ 2:15-16)

<u>ሴቲቱና ባልዋ</u>

| | |
|---|---|
| የዓይን አምሮት | ለዓይን እንደሚያስጐመጅ |
| የሥጋ ምኞት | ለመብላት ያማረ |
| የሕይወት ትምክህት | ለጥበብም መልካም እንደሆነ አየች |

ክርስቶስ

- ክርስቶስ የሰው ዘሮችን ሁሉ በመወከል ታዘዘ በመሆኑም በእርሱ መታዘዝ ምክንያት የሚያምኑበት ሁሉ ጽድቅ ይቆጠርላቸዋል:: (ሉቃ 4:1-13, ሮሜ 5:18-19)

| | |
|---|---|
| የዓይን አምሮት | የዓለምን ነገሥታት ክብራቸውን አሳየው |
| የሥጋ ምኞች | በራበው ጊዜ ድንጋዩን እንጀራ አድርገው አለው |
| የሕይወት ትምክህት | የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንክ ከዚህ ወደታች ራስህን ጣል አለው:: |

- ክርስቶስ የኋለኛው አዳም ነው (1ቆሮ 15:45)
- አዳም ፊተኛው ሰው ነበረ ክርስቶስ ሁለተኛው ሰው ነው::

| የፊተኛው አዳም (አዳም) (ሮሜ 5:18-19) | የኋለኛው አዳም (ክርስቶስ) |
|---|---|
| - አልታዘዘም | - ፈጽሞ ታዘዘ |
| - የበደሉ መጠን ከኋለኛው አዳም የጽድቅ መጠን እጅግ በጣም ያነሰ ነው:: | - የጽድቁ ብዛት ከፊተኛው አዳም ይልቅ እጅግ በጣም የበዛ ነው:: |
| - በዚህ ምክንያት ሰዎች ሁሉ ይሞቱ ነበር:: | - በዚህ ምክንያት ሰዎች በሕይወት ለዘለዓለም ይነግሳሉ:: |

## ለ. በምትክነት ለመሞት እና መስዋዕት ለመሆን

- አምላክ አይሞትም በመሆኑም የሚሞት ሥጋ መልበስ አስፈለገው (ዮሐ 1:14)
- በሞቱ አማካይነት ሥልጣናትን ሊሽር በሥጋና በደም መካፈል ነበረበት (ዕብ 2:16-17)
- በመሆኑም የብሉይ ኪዳን መስዋዕቶችን ሁሉ በመተካት ፍጹም የሆነ የኃጢአት ሥርየትን ለመስጠት መሰዋት ነበረበት::
  (ዮሐ 1:29, ዕብ 9:22-28, ዕብ 10:1-18)
- በመሆኑም ኢየሱስ የሞተው በራሱ ምክንያት ሳይሆን በሰዎች ምክንያት በመሆኑ የእርሱ ሞቱ የምትክነት ሞት (Substitutionary death) ይባላል::

## ሐ. በእግዚአብሔርና በሰው መካከል መካከለኛ (ሊቀ ካህናት) ለመሆን ነው::

- እርሱ ፍጹም አምላክ በመሆኑ በእግዚአብሔር ፊት ሊቆም የሚችል፣ ፍጹም ሰው በመሆኑ የአማኞችን ድካም የሚረዳ ሆኗል (1ጢሞ 2:5)
- በሰውነቱ ምክንያት የተፈተነ ነውና ሊራራልን ይችላል (ዕብ 2:18, 4:15-16)

# ክፍል ፪

# የኢየሱስ ክርስቶስ ፍፁም አምላክነት (መለኮትነት)

አምላክነቱ ከሥጋው የተዋሀደበት ትምህርት "ምሥጢረ ሥጋዌ" ወይም "ትሥጉት" Incarnation ይባላል:: ምሥጥረ ሥጋዌ አምላክ ከሥጋ ጋር የተዋሀደበት መለኮታዊ አሠራሩ ነው:: በመሆኑም ክርስቶስ ሙሉ በሙሉ ሰው ብቻ ሳይሆን ሙሉ በሙሉ ደግሞ ፍፁም አምላክ ነው::

## <u>ማረጋገጫ</u>

### 2.1. የተጠቀሱ መጠሪያ ስያሜዎች

**ሀ. እግዚአብሔር (Theos) (ዮሐ 1:1-3)**

- ይህ ቃል ፍፁም መለኮት ለሆነው ለእግዚአብሔር የምንጠቀምበት ቃል ሲሆን በሚከተሉት ጥቅሶች ውስጥ ሁሉ "ቴዎስ" የተጠቀሰው ለኢየሱስ ክርስቶስ መለኮታዊ ማንነት ነው::

  **(ዮሐ 1:1, 20:28, ሮሜ 9:5, ቲቶ 2:13, ዕብ 1:8 2ጴጥ 1:1)**
- የብሉይ ኪዳን ትንቢቶችም እርሱ አምላክ መሆኑን በግልፅ አሳይተዋል

  **(ኢሳ 9:6, መዝ (110):1, (45):6, (102):2)**

**ለ. ጌታ (Kyrios)**

- በክርስቶስ ዘመን ይህ ቃል በግሪክ ሰባው ሊቃውንት መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሙበት በዕብራይስጡ ያህዌህ ወይም ጀሆቫህ ለሚለው የአምላክ ስም ነው::
- ኪሪዮስ በግሪኩ ብለይ ኪዳን ውስጥ ጌታ እግዚአብሔር ለሚለው ስያሜ 6,814 ጊዜ ተጠቅሷል:: ይኸው ኪሪዮስ ጌታ ኢየሱስ የሚጠራበት "ጌታ" የሚለው ቃል ነው:: ስለሆነም ማንኛውም ግሪካዊ አንባቢ "ጌታ" ኢየሱስ የሚለውን ቃል የሚረዳው የሁሉ ነገር ፈጣሪና፣ የፍጥረቱ ሁሉ መጋቢ እና አስተዳዳሪ አድርጐ ነው::

  **(ሉቃ 2:11, ማቴ 3:3 - ኢሳ 40:3, ማቴ 22:44, 1ቆሮ8:6, 12:3)**

**ሐ. ኢየሱስ የተጠቀማቸው ቃላቶች እና ስያሜዎች**

- አብርሃም ሳይወለድ እኔ አለሁ "I am" **(ዮሐ 8:58)**

  የአይሁድ መምህራን እኔ የሚለውን ስያሜ የሚያያይዙት በዘፀአት **3:14** ላይ ከተጠቀሰው ስም ጋር ነው "I am who I am" ስለሆነም ሊወግሩት ድንጋይ አነሱ ቁ **59**

- ✓ አልፋና ኦሜጋ እኔ ነኝ (ራዕ 22:13)
  መጀመርያና መጨረሻ የሚለው ስያሜ መለኮታዊ ማንነትን የሚገልጥ ሲሆን በብሉይ ኪዳን የተጠቀሰው ለእግዚአብሔር ነው:: (ኢሳ 44:6)
- ✓ የእግዚአብሔር ልጅ
  የእግዚአብሔር የባህርይ ልጅ እና እግዚአብሔር የሆነ ማለት ነው::
  ማቴ 11:25-30, 17:5, 1ቆሮ 15:28, ዕብ 1:1-3, 5, 8

- አባት የሚሠራውን ሁሉ ልጁም ይሠራዋል ዮሐ 5:20-22, 25, 10:17, 16:15

**መ. ኢየሱስ/ አማኑኤል**

በዕብራይስጥ "Yehoshuah":: ያህ የእግዚአብሔር ስም ሲሆን "ዬሆሹዋ" ማለት እግዚአብሔር መድኃኒት ነው ማለት ነው እንዲሁም አማኑ-ኤል፣ ኤል - አምላክ ማለት ስለሆነ "አምላክ ከእኛ ጋር" እንደማለት ነውና እርሱ "እግዚአብሔር አምላክ" ነው::

## 2.2 የኢየሱስ መለኮታዊ ባህርያት (Divine Essences)

መለኮታዊ ባህርያት ማለት መለኮት ብቻ ሊኖረው የሚችለው የትኛውም ፍጥረት የማይኖረው የአምላክ መታወቂያና መገለጫ ባህርያቶቹ ናቸው::

**ሀ. ሁሉን ማድረግ ይችላል (Omnipotent)**

ማዕበል በቃሉ አዟል ማቴ 8:26-27

ዳቦና አሣ አበርክቷል (ማቴ 14:19)

ውኃ ወደወይን ጠጅ ቀይሯል ዮሐ 2:1-11

**ለ. ዘለዓለማዊ ነው ዮሐ 8:58, ራዕ 22:13**

**ሐ. ሁሉን ያውቃል (Omniscience)**

የሰዎችን ሀሳብ (ማር 2:8) አሳልፎ የሚሰጠውን (ዮሐ 6:64) (ዮሐ 2:25, 16:30)

**መ. በሁሉ ቦታ ይገኛል (Omnipresence) (ማቴ 18:20, 28:20)**

**ሠ. ሉዓላዊ ሥልጣን አለው (Sovereignity)**

ኃጢአትን ይቅር ማለት (ማር 2:5-7) እግዚአብሔር እንዲህ ይላችኋል ሳይሆን እኔ ግን እላችኋለሁ ይላል (ማቴ 5:22, 28, 32, 34, 39, 44)

**ረ. አምልኮን ይቀበል ነበር**

ከመላዕክት(ዕብ 1:6 ራዕ 5:6-19) ከሰዎች (ዮሐ 9:38) ጉልበት ሁሉ (ፊል 2:9-11) በአጠቃላይ ኢየሱስ ክርስቶስ የመለኮት ሙላት ሁሉ የተገለጠበት ነው:: (ቈላ 1:19, 2:9)

## 2.3 ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም አምላክ የመሆኑ አስፈላጊነት

ሀ. የሚያምኑበትን ሁሉ ፍርዳቸውን ሊሸከም እና ሊያስወግድ የሚችል ፍጹም አምላክ የሆነ ማንነት ብቻ ነው።

ለ. ደህንነት ከእግዚአብሔር ብቻ ነው (ዮናስ 2:10)

ሐ. ፍጹም አምላክ እና ፍጹም ሰው የሆነ ማንነት ብቻ ነው በሰውም በእግዚአብሔር መካከል መካከለኛ መሆን የሚችለው (1ጢሞ 2:5)

በመሆኑም ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ ባይሆን ኖሮ ደህንነትም፣ ክርስትናም ፈጽሞ አይኖሩም ነበር።

"ወልድን የሚክድ ሁሉ አብ የለውም" 1ዮሐ 2:23

"በክርስቶስ ትምህርት ለማይኖር አምላክ የለውም" 2ዮሐ ቁ9


## ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም አምላክ ነው

| | |
|---|---|
| **ሀ. እግዚአብሔር ፈጣሪ ነው::**<br>ዘፍ 1:1, ዘፍ 2:7, ኢዮ 33:4, መዝ 33:6, መዝ 104:30, ኢሳ 40:28, ኢሳ 44:24, ኢሳ 45:11-18, ሚል 2:10 | **ኢየሱስ ክርስቶስ ፈጣሪ ነው::**<br>ዮሐ 1:3, 10, 1ቆሮ 8:6, ኤፌ 3:9, ቈላ 1:12-17, ዕብ 1:8-12, ራዕ 4:8-11, ራዕ 10:6, ራዕ 14:6-7, ራዕ 21:5-7, ራዕ 22:3, ራዕ 7:17 |
| **ለ. እግዚአብሔር አዳኝ ነው**<br>መዝ 78:34-35, ኢሳ 47:4, ኢሳ 44:6,24 43:3-11, 45:21, ኢሳ 49:26, መዝ 106:21, ሉቃ 1:46-47, 1ጢሞ 1:1, ቲቶ 1:1-4, 1ጢሞ 4:10, ቲቶ 2:10-13 | **ኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝ ነው**<br>1ዮሐ 4:14, 1ጴጥ 2:21-24, ሐዋ 20:28, ገላ 3:13, ሉቃ 24:21-29, ሉቃ 2:10-11, ዮሐ 4:40-42, ሐዋ 13:23, ፊል 3:20, 1ጢሞ 1:1,2, ቲቶ 1:4, 1ጴጥ 1:10, ይሁዳ 25 |
| **ሐ. እግዚአብሔር ዳግም ይመጣል**<br>ዘካ 14:3-5, 1ተሰ 4:13-18, መዝ 50:1-6 | **ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ይመጣል**<br>1ተሰ 3:11-13, ማቴ 25:31-46, ቲቶ 2:11-13, ራዕ 19:11, 16 |
| **መ. እግዚአብሔር ዓለት ነው**<br>ዘዳ 32:3-4, 1ሳሙ 2:2, 2ሳሙ 22:2, መዝ 18:2, መዝ 31:1-4, መዝ 78:35, መዝ 89:26, ኢሳ 17:10 | **ኢየሱስ ክርስቶስ ዓለት ነው**<br>ማቴ 16:17-19, ሐዋ 4:11-12, ዘኍ 20:1-11, 1ቆሮ 10:4, ኢሳ 28:16, ኤፌ 2:20-22, 1ጴጥ 2:6-8 |
| **ሠ. እግዚአብሔር መጀመርያና መጨረሻ ነው**<br>ኢሳ 41:4, ኢሳ 43:10-11, ኢሳ 44:6-8 ራዕ 1:8 | **ኢየሱስ ክርስቶስ መጀመርያና መጨረሻ ነው**<br>ራዕ 1:17, ራዕ 22:13 |
| **ረ. እግዚአብሔር "እኔ ነኝ" ይላል**<br>ዘፀ 3:13-14, ኢሳ 43:10, ኢሳ 43:25 | **ኢየሱስ "እኔ ነኝ" ይላል**<br>ዮሐ 18:5-8, ራዕ 1:17-18, ራዕ 8:24-28 |
| **ሰ. እግዚአብሔር ንጉሥ ነው**<br>መዝ 47:2, 6, መዝ 44:4, መዝ 74:12, ዘካ 14:9, ኢሳ 44:6, ኤር 10:10 | **ኢየሱስ ንጉስ ነው**<br>ማቴ 2:1-6, ሉቃ 19:35-38, ሉቃ 23:3, ዮሐ 18:37, ዮሐ 19:21, 1ጢሞ 6:13-16, ራዕ 15:1-4, ራዕ 19:11-16 |
| **ሸ. እግዚአብሔር እረኛ ነው**<br>መዝ 23:1, ኢሳ 40:10-11, ኢሳ 10:3 | **ኢየሱስ እረኛ ነው**<br>ዮሐ 10:8-12, 1ጴጥ 2:21-25, ዕብ 13:20, 1ጴጥ 5:4 |

## ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የተሳሳቱ አመለካከቶች

### ሀ. አፖሊናሪያኒዝም፡- ኢፖሊናሪስ በ361 የሎዶቂያ ጳጳስ ነበር

ኢየሱስ አካሉ የሰው ቢሆንም ነገር ግን የሰው ሕሊና፣ እና የሰው ባህርያት አልነበሩትም የሚል ነበር፣ መለኮታዊ ባህርያት ብቻ በሰውነቱ ወስጥ ነበረው ይል ነበር፡፡





* ትምህርቱ በ362 ዓ.ም. በአሌክሳንደርያ ጉባኤ፣ በ381 ዓ.ም. በኮንስታንቲኖኘል ጉባኤ

ተወግዟል፡፡

### ለ. ኔስቶሪያኒዝም፡- ሁለት የተለያዩ ማንነቶች በክርስቶስ ውስጥ ነበሩ የሚል ነው፡፡

ይህም ማለት ሰብዓዊ ማንነት እና መለኮታዊ ማንነት ተነጣጥለው በአንዱ ክርስቶስ ውስጥ ነበሩ ብሏል፡፡ ኔስቶሪየስ በ428 ዓ.ም. በአንጾኪያ ታዋቂ ሰባኪና የኮንሲታንቲኖኘል ጳጳስም ሆኖ ነበር፡፡




### ሐ. ሞኖፊሲቲዝም/ኢዩቲይኪዝም፡-

አውጣኬ ከ378-454 ገደማ በኮንስታንቲኖኘል የነበረ የገዳም አለቃ ነው፡፡ ክርስቶስ አንድ ባህሪይ ብቻ ነበረው እንጂ ፈጽሞ ሁለቱም ባህሪያት አልነበሩትም አለ ሰብዓዊ ባህርያቱ በሙሉ ከመለኮታዊ ባህርያቱ ጋር እርስ በርስ ተዋዋጡ ብሎም አስተማረ፡፡ በመሆኑም አዲስ የሆነ ባህርይ ነበረው ይል ነበር፡፡



## አራቱ ወንጌሎች የኢየሱስን ማንነት በዋነኛነት የገለጹበት መንገድ

ማቴዎስ:- ኢየሱስ የአይሁድ ንጉሥ እና መሲህ
ንጉሥ ስምንት ጊዜ፣ የዳዊት ልጅ ዘጠኝ ጊዜ ተጽፏል
(ማቴ 2:2, 21:5, 25:34, 40, 27:11, 29,37,42)
(ማቴ 1:1, 9:27, 12:23, 15:22, 20:30-31, 21:9, 15, 22:42)

ማርቆስ:- ኢየሱስ ተአምራትና ድንቅ አድራጊ፣ የሰዎችና የእግዚአብሔር አገልጋይ
(ማር 6:2, 10:45)

ሉቃስ:- የሰው ልጅ:- የሰው ልጆች ወዳጅ፣ የጠፉትን የሚፈልግ
(ሉቃ 19:10, 10:30-37, 15:4-7, 15:11-32, 18:10-14, 19:2-10, 23:39-43)

ዮሐንስ:- በየምዕራፉ ላይ በተለያየ ማንነት ገልጾታል
ምዕራፍ 1 የእግዚአብሔር ልጅ # 1-14
ምዕራፍ 2 የሰው ልጅ # 1-10
ምዕራፍ 3 መለኮታዊ መምህር # 2-21
ምዕራፍ 4 ነፍሳትን የሚጠራ # 7-29
ምዕራፍ 5 ታላቁ ሀኪም # 1-9
ምዕራፍ 6 የሕይወት እንጀራ # 32-58
ምዕራፍ 7 የሕይወት ውኃ ምንጭ # 37
ምዕራፍ 8 የኃጢአተኞች እና የደካሞች ደገፉ # 3-11
ምዕራፍ 9 የዓለም ብርሃን # 1-39
ምዕራፍ 10 መልካም እረኛ # 1-16
ምዕራፍ 11 የሕይወት ራስ # 1-44
ምዕራፍ 12 ንጉሥ # 12-15
ምዕራፍ 13 አገልጋይ # 1-10
ምዕራፍ 14 አጽናኝ # 1-3
ምዕራፍ 15 የወይን ግንድ # 1-16
ምዕራፍ 16 መንፈጽ ቅዱስን የሚሰጥ # 1-15
ምዕራፍ 17 ታላቁ ጸሎተኛ እና አማላጅ # 1-26
ምዕራፍ 18 የመከራ ተካፋይ # 1-11
ምዕራፍ 19 የተሰቀለው አዳኝ # 16-19
ምዕራፍ 20 ሞትን ያሸነፈ # 1-31
ምዕራፍ 21 ንስሐ የሚገቡትን የሚጠግን # 1-17

## የኢየሱስ ክርስቶስ በ66ቱ መጽሐፍት በዋነኛነት የተገለጠበት ማንነት

| የመጽሐፍት ስም | የኢየሱስ ክርስቶስ ማንነት |
|---|---|
| 1. ኦሪት ዘፍጥረት | - ፈጣሪ አምላካችን |
| 2. ኦሪት ዘፀአት | - የፋሲካችን በግ |
| 3. ኦሪት ዘሌዋውያን | - የኃጢአታችን መስዋዕት |
| 4. ኦሪት ዘኍልቁ | - በዓላማ ላይ የተሰቀለ |
| 5. ኦሪት ዘዳግም | - እውነተኛው ነቢያችን |
| 6. መጽሐፈ ኢያሱ | - የደህንነታችን ራስ እና መሪ |
| 7. መጽሐፈ መሳፍንት | - ነፃ አውጪ መስፍናችን |
| 8. መጽሐፈ ሩት | - የሚቤዠን የቅርብ ወዳጅ |
| 9,10. መጽሐፈ ሳሙኤል 1ኛ ና 2ኛ | - ንጉሣችን |
| 11,12,13,14, ነገሥትና ዜና መዋዕል | - ንጉሣችን እና ነቢያችን |
| 15. መጽሐፈ ዕዝራ | - የፈረሰውን አዳሽ |
| 16. መጽሐፈ ነህምያ | - የፈረሰውን ጠጋኝ |
| 17. መጽሐፈ አስቴር | - ስለእኛ የሚማፀን |
| 18. መጽሐፈ ኢዮብ | - የሚቤዠን |
| 19. የመዝሙር መጽሐፍ | - ሁሉ በሁሉ የሆነ |
| 20. መጽሐፈ ምሳሌ | - ጥበባችን |
| 21. መጽሐፈ መክብብ | - የነገሮች ሁሉ ፍፃሜና መደምደሚያ |
| 22. መኃልይ መኃልይ | - የነፍሳችን ወዳጅ |
| 23. ትንቢተ ኢሳያስ | - የሚመጣው መሲህ |
| 24, 25. ትንቢተ ኤርሚያስና ሰቆቃው | - ፃድቅ ቁጥቋጥ |
| 26. ትንቢተ ሕዝቅኤል | - የሰው ልጅ |
| 27. ትንቢተ ዳንኤል | - የሚያደቅቅና የሚፈጭ ድንጋይ |
| 28. ትንቢተ ሆሴዕ | - ያፈገፈጉትን የሚመልስ |
| 29. ትንቢተ ኢዮኤል | - የሚያድስ የሚመልስ |
| 30. ትንቢተ አሞጽ | - ሰማያዊ ባል |
| 31. ትንቢተ አብድዩ | - መድኃኒታችን |
| 32. ትንቢተ ዮናስ | - ትንሣኤና ሕይወታችን |
| 33. ትንቢተ ሚክያስ | - እውነተኛና ታማኝ ምስክር |
| 34. ትንቢተ ናሆም | - በመከራ ጊዜ መሸሸጊያ |
| 35. ትንቢተ ዕንባቆም | - የደህንነታችን አምላክ |
| 36. ትንቢተ ሶፎንያስ | - ቀናተኛ አምላክ |
| 37. ትንቢተ ሐጌ | - በአህዛብ ሁሉ የተመረጠ |
| 38. ትንቢተ ዘካርያስ | - ፃድቅ ቁጥቋጥ |
| 39. ትንቢተ ሚልኪያስ | - የፅድቅ ፀሐይ |

40. የማቴዎስ ወንጌል - መሲህና ንጉሥ
41. የማርቆስ ወንጌል - የእግዚአብሔርና የሕዝቡ አገልጋይ
42. የሉቃስ ወንጌል - የሰው ልጅና፣ የጠፉትን የሚፈልግ
43. የዮሐንስ ወንጌል - የእግዚአብሔር ልጅ
44. የሐዋርያት ሥራ - ሕያው ጌታ
45. የሮሜ መልዕክት - ጽድቃችን
46. የቆሮንቶስ መልዕክት - ጌታችን
47. 2ኛ የቆሮንቶስ መልዕክት - ብቃታችን
48. የገላትያ መልዕክት - ነፃነታችን
49. የኤፌሶን መልዕክት - የእኛ ሁሉ ነገራችን
50. ፊልጵስዩስ መልዕክት - ደስታችን
51. የቈላስይስ መልዕክት - ሕይወታችን
52. 1ተሰሎንቄ መልዕክት - ዳግም የሚመጣው ተስፋ
53. 2ተሰሎንቄ መልዕክት - ተመልሶ የሚመጣልን ጌታ
54. 1 ጢሞቴዎስ መልዕክት - መምህራችን
55. 2 ጢሞቴዎስ መልዕክት - የምንመለከተው ምሳሌያችን
56. የቲቶ መልዕክት - የምንለማመደው ምሳሌያችን
57. የፊልሞና መልዕክት - ጌታችንና መምህራችን
58. የዕብራውያን መልዕክት - በዙፋኑ ፊት የቆመ ሊቀካህናችን
59. የያዕቆብ መልዕክት - የአኗኗር ተምሳሌት
60. 1ጴጥሮስ መልዕክት - የከበረ የማዕዘን ራስ ድንጋይ
61. 2ጴጥሮስ መልዕክት - ብርታትና ኃይላችን
62. 1ዮሐንስ መልዕክት - ሕይወታችን
63. 2ዮሐንስ መልዕክት - እውነት
64. 3ዮሐንስ መልዕክት - መንገድ
65. የይሁዳ መልዕክት - የእምነታችን ጠባቂ
66. የዮሐንስ ራዕይ - ድል አድራጊው ንጉሣችን

## ስለኢየሱስ ክርስቶስ የተነገሩ ትንቢቶችና በእርሱ ስለ መፈጸማቸው

| ትንቢቶች | | መፈጸማቸው |
|---|---|---|
| ዘፍ 3:15 | የሴቲቱ ዘር | ገላ 4:4, ሉቃ 2:7 |
| ዘፍ 18:18, 12:3 | የአብርሃም የተስፋ ቃል ዘር | ሐዋ 3:25, ማቴ 1:1, ገላ 3:15-18 |
| ዘፍ 17:19 | የይስሐቅ የተስፋ ቃል ዘር | ማቴ 1:2, ሉቃ 3:34 |
| ዘኁ 24:17,ዘፍ 28:14 | የያዕቆብ የተስፋ ቃል ዘር | ሉቃ 3:34, ማቴ 1:2 |
| ዘፍ 49:10 | ከይሁዳ ነገድ የሆነ | ሉቃ 3:33, ማቴ 1:2-3, ራዕ 5:5 |
| መዝ(89):28-37, ኢሳ 9:7, 11:1-5 | በዳዊት ዙፋን የሚቀመጥ ዘር | ማቴ 1:1, ሉቃ 1:32 |
| ሚክ 5:2 | የትውልድ ሥፍራ | ማቴ 2:1, ሉቃ 2:4-7 |
| ዳን 9:25 | የልደት ጊዜው | ሉቃ 2:1-7 |
| ኢሳ 7:14 | በድንግልና መወለዱ | ማቴ 1:18, ሉቃ 1:26-35 |
| ኤር 31:15 | የሕፃናት መገደል | ማቴ 2:16-18 |
| ሆሴ 11:1 | ወደግብጽ መሸሽ | ማቴ 2:14, 15 |
| ኢሳ 9:1-2 | የገሊላ አገልግሎቱ | ማቴ 4:12-16 |
| ዘዳ 18:15 | ታላቅ ነቢይነቱ | ዮሐ 6:14, ሐዋ 3:19-26 |
| መዝ 110:4 | መልከጼዴቂያዊ ክህነቱ | ዕብ 6:20, 5:5-6, 7:15-17 |
| ኢሳ 53:3 | በአይሁድ ተቀባይነት ማጣቱ | ዮሐ 1:11, 5:43, ሉቃ 4:29, 17:25 |
| ኢሳ 11:2-4 | ባህሪያቱ | ሉቃ 2:52, 4:18 |
| ዘካ9:9 | እንደንጉሥ ወደ ከተማይቱ መግባቱ | ዮሐ 12:13-14, ማነ 21:1-11 |
| መዝ 41:9 | በባልንጀራው መከዳቱ | ማር 14:10 ማቴ 26:14-16 |
| ዘካ 11:12 | በሠላሳ ብር መሸጡ | ማቴ 26:15, ማቴ 27:3-10 |
| ዘካ 11:13 | ገንዘቡ ለሸክላ ሠሪ መሬት እንደተሰጠ | ማቴ 27:6-10 |
| መዝ 109:7-8 | የይሁዳ ሥፍራ በሌላ መተካቱ | ሐዋ 1:18-20 |
| መዝ 27:12, 35:11 | የሐሰት ምስክሮች | ማቴ 26:60-61 |
| ኢሳ 53:7 | ሲከሱት ዝም ማለቱ | ማቴ 26:62-63, ማቴ 27:12-14 |
| ኢሳ 50:6 | መመታቱና መትፋታቸው | ማር 14:65, 15:17, ዮሐ 191-3 |
| መዝ 69:4, 109:3-5 | ያለምክንያት መጠላቱ | ዮሐ 15:23-25 |
| ኢሳ 53:4-5, 6,12 | ታላቅ መከራን መቀበሉ | ማቴ8:16-17, ማቴ 27, ማር 14, |

| | | |
|---|---|---|
| ኢሳ 53:12 | ከኃጢአተኞች ጋር መሰቀሉ | ማቴ 27:38 |
| መዝ 22:16 | እጁና እግሩ መቸንከሩ | ዮሐ 20:27, ዮሐ 19:37 |
| መዝ 22:6-8 | እንደሚሳገዱበት | ማቴ 27:39-40 |
| መዝ 69:21 | ሐሞትና የወይን ጠጅ እንደሚቀምስ | ዮሐ 19:29, ማቴ 27:34, 48 |
| መዝ 22:8 | የሚሳገዱበት ቃል | ማቴ 27:43 |
| መዝ 109:4 | ለጠላቶቹ እንደሚጸልይ | ሉቃ 23:34 |
| ዘካ 12:10 | ጐኑ በጦር እንደሚወጋ | ዮሐ 19:34 |
| መዝ 22:18 | በልብሱ ላይ እጣ እንደሚጣጣሉ | ማር 15:24 |
| መዝ 34:20 | አጥንቱ እንደማይሰበር | ዮሐ 19:33 |
| ኢሳ 53:9 | ከባለጠጐች ጋር በመቃብሩ እንደሚሆን | ማቴ 27:57-60 |
| መዝ 16:10 | ትንሣኤው | ማቴ 28:9, ሉቃ 24:36 |
| መዝ 68:18 | እርገቱ | ሉቃ 24:50-51, ሐዋ 1:9 |

## የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ የምድር ሕይወት ዘመን ግምት

ልደቱ በ4 ወይም 5 ቅ.ክ.

ወደ ግብጽ ሽሽት በ4 ወይም በ5 ቅ.ክ.

ከግብጽ መልስ ከ3 ወይመ በ4 ቅ.ክ.

በልጅነቱ ቤተመቅደስ የሄደበት ጊዜ ምናልባት በ8 ዓ.ም.

የዮሐንስ መጥምቁ አገልግሎት የተጀመረበት ጊዜ ምናልባት በ26 ዓ.ም.

ኢየሱስ በዮሐንስ የተጠመቀበት ጊዜ ምናልባት በ26 ዓ.ም.

ጌታ ኢየሱስ አገልግሎት የጀመረበት ጊዜ ምናልባት በ26 ዓ.ም.

የጌታ ኢየሱስ ዝናው የወጣበት ጊዜ ምናልባት በ27 ዓ.ም.

ተቃውሞ እየበረታበት የመጣበት ጊዜ ምናልባት በ28 ዓ.ም.

ሞቱና ትንሣኤው ምናልባት በ29 ወይም በ30 ዓ.ም. የመጀመርያው ወር

☞ ዳዊት ፋሲል

ስ.ቁ. 0917804407

ፖ.ሣ.ቁ. 67 ጅማ

E-mail – besodiyah@gmail.com ወይም

niguye2004@yahoo.com